# <u>ቆሜ ነው እምሞተው</u>!!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

አልጠብቅም ሞትን ተኝቼ ባልጋዬ ፤
እኔው እሄዳልለሁ ፈረሴን ቹ ! ብዬ ፤
በ'ንባ አልታጠብም ቁጭ ብዬ አላለቅስም ፤
ጉልበቴን አጥፌ አልንበረከክም ፤
አልጠብቅም እሱን ወደኔ እስቲመጣ ፤
እኔው እሄዳለሁ ወደሱ እንዳይመጣ ፤
ኩራቴን ይረዳው ድፍረቴን ይወቀው ፤
ተጋድሜ አልሞትም ቆሜነው እምሞተው !!

አልፈልግም ዋሻ የምደበቅበት ፤
አያሻኝም ጢሻ የምሸሸግበት ፤
አልሰብርም አንገቴን አላዞርም ፊቴን ፤
አይዝልም ጉልበቴ አላጥፈውም ክንዴን ፤
እጠብቀዋለሁ ደረቴን ነፍቼ ፤
በኩራት በድፍረት ጋሻዬን መክቼ ፤
አልንበረከክም ቆሜነው እምሞተው ፤
የጀግና ልጅ ጀግና መሆኔን ይወቀው !!

አልጠብቅም ሞትን ማታ በጨለማ ፤
እንዲወስደኝ ብዬ ሰው ሳያይ ሳይሰማ ፤
አለምንም ከቶ ዛሬን እንዲተወኝ ፤
ዘግይቶ እንዲመጣ ዕድሜ እንዲለግሰኝ ፤
ያልጋ ቁራኛ አርጎ እያጨማለቀ፤
ሞት መጥቶ እስቲወስደኝ እያመናጨቀ ::

ጭራሹን !
እጠብቀዋለሁ በጠራራ ፀሐይ ፤
መሃላዬ ይሁን ቃል ለምድር ለሰማይ ፤
ቆሜነው እምሞተው እንደ ክርስቶስ
ዳግም ድል አድርጌ እስክነሳ ድረስ ::

**ይጥልልኝ ብዬ ትርፍራፊ እድሜ ፤**
**አልጠብቅም ሞትን እኔ ተጋድሜ ፤**
**እሄዳለሁ እኔ ወደሱ እንዳይመጣ ፤**
**ግንባሬን አላጥፍም የመጣው ቢመጣ ፤**
**ተኝቼ አልጠብቅም ሞት መጥቶ እስቲወስደኝ ፤**
**እኔው እሄዳለሁ በቁሜ እንዲያገኘኝ ፤**
**ለመኖር ጓጉቼ አልንበረከክም ፤**
**ዛሬን ተወኝ ብዬ አልለማመጥም ፤**
**አልንበረከክም ቆሜነው እምሞተው ፤**
**የጀግና ልጅ ጀግና መሆኔን ይወቀው !!**

*አንድ ቀን*

*ለወጣት መምህር የኔሰው ገብሬ፣ እንዲሁም የአገራቸውን ውድቀት፤ የወገናቸውን ድቀት፤ እንቢ በማለት፡ ለእኩልነት፤ ለአንድነት፤ ለዲሞክራሲና ለፍትህ መከበር በመታገል ለወደቁ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን በሙሉ መታሰቢያ ትሁንልኝ፡፡*

**To Remember the young Ethiopian Teacher Yenesew Gebré and Ethiopian Martyrs of June and November 2005.**